# ምን ሰራ ለአማራ?

ሰላም ሰፍኗል ባገር ፣ ነጋ ጠባ ወሬ
ይደረጋል ብቻ ፣ አያፈራ ፍሬ
ስቃዩ በርትቶ ፣ ከትላንቱ ዛሬ
በስሎ እማይጎመራ ፣ እንዳለፈው ጥሬ
ሰላም ሰላም ቢባል ፣ ቢግቱት ባቦሬ
ጠብ አይል ላማራው ፣ ጥም አይቆርጥ ቅራሬ ።

ያለፈን አውግዘን ፣ ዛሬ አዲስ ቢመጣ
መተካካት እንጂ ፣ ለውጥን አላመጣ
በነገደ አማራ ፣ መዓት ሲወርድ ቁጣ
እያፈናቀሉት ፣ ካገር እየወጣ
መከራው ፀንቶበት ፣ አይቀጡ ሲቀጣ
የይቅርታ ስብከት ፣ የሃሰት ለበጣ
ቀንም ማታ ወሬ ፣ መቼም አያዋጣ ።

ከወገኑ ጋራ ፣ ያገኘውን በልቶ
ዘር ብሄርን ሳይለይ ፣ ከሁሉ ተጋብቶ
ጎንበስ ቀና እያለ ፣ ለኢትዮጵያ ለፍቶ
ወራሪ ቢመጣ ፣ ጠላትን መክቶ
ላገሩ የሰራው ፣ ውለታው ተረስቶ
አባቶች ያቆሙት ፣ ወግ ስርዓት ቀርቶ
የጥንት ህብረታችን ፣ ታሪክ ተዘንግቶ
እንዴት ዛሬ አማራ ፣ ይኑር አንገት ደፍቶ ።

ገና በይሆናል ፣ በህልም እንጀራ ተሰፋ
በደል እንዳይታይ ፣ ህዝብ እንዲያንቀላፋ
የፍቅር ይቅርታ ፣ ጡሩምባ ሲያስነፋ
አማራው ከቀዬው ፣ ሲነቀል ሲገፋ
ከትላንት በባሰ ፣ በደል እየከፋ
ምን አቋም ወሰዱ ፣ አማራን ድገፋ
ምነው ለሱ ደራሽ ፣ የሚሟገት ጠፋ።

ዳር ድንበር ጠባቂ ፣ ያገር ባላደራ
የትውልድ አንጋፋ ፣ የነፃነት አውራ
እንኳንስ ወገኑን ፣ አፍሪካን ያኮራ
አጥንቱን ከስክሶ ፣ ደሙን እንዳልዘራ
ላገሩ እንዳልሞተ ፣ አንበሳው አማራ
ተዘልዝሎ ስጋው ፣ አርደውት በካራ
ገለው እሬሳውን ፣ ሲያሰጡት ላሞራ
በዘመነ አብይ ፣ አብይ ግፍ ሲሰራ
ጠ/ሚኒስትሩ ፣ ምን ሰራ ለአማራ ።?

ታዛቢው

June 8, 2018